

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከሴፕቴምበር 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከሴፕቴምበር 21-30 እና ከኦክቶበር 1-10/2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያወቹ ቀናቶች ላይ ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም ዝናቡ በስርጭትም ሆነ በመጠን በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አከባቢዎቹን ያዳረሰ የዝናብ ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 30.1፣ 37.4፣ ባህርዳር 43.4፣ ጎሬ 44.3፣ ነቀምቴ 37.4፣ 43.4፣ አይራ 47.8፣ 44.5፣ 32፣ ሐሮማያ 44.5፣ አምደወርቅ 73.4፣ አንገር ጉትን 34፣ 46.2፣ አርሲ ሮቤ 33.8፣ በደሌ 44.4፣ ቡለን 40.2፣ ጨዋቃ 48፣ ደብረ ታቦር 34.5፣ 30፣ ፍቼ 35.8፣ ፉኙዶ 82.5፣ 56፣ ገለምሶ 37.2፣ ጊዳ አያና 33፣ 52.9፣ ጊምቢ 42.5፣ 31.3፣ ጃሬ 38.2፣ ኮንሶ 38.7፣ ማንኩሽ 45፣ መተማ 30፣ 38.2፣ ሞጣ 40.2፣ ሰንቃጣ 31፣ ሽርቆሌ 36.3፣ አታንጎ 49፣ 54.5፣ ቦርቃ 44.8፣ ጨፌ ዶንሳ 37.3፣ ደራ 35.5፣ ጊነገር 35.6፣ ጎሮ 36፣ ሃሮ 30.4፣ 40.2፣ 50.1፣ 40.4፣ ቅዳሜ ገበያ 52.8፣ 34.8፣ ኮበን 35፣ መሆኒ 30.9፣ ኦሞ ናዳ 40.2፣ ኦንጋ 42፣ ተረኮዲ 33.8፣ ያንፋ 32.8፣ 40.3፣ ያዮ 41.6፣ ዩጪላ 40.3፣ እዳግ አርቢ 42.2፣ እንዲሁም ከርሳ 35.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በሀምሳ አምስት (55) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 41.6-82.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ፉኙዶ፣ አምደ ወርቅ፣ ማንኩሽ፣ ደራ፣ አታንጎ፣ ቡለን፣ ጊዳ አያና፣ ቅዳሜ ገበያይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute





**ምስል፡1 ከሴፕቴምበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው**

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ41-220 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የዋግ ህምራ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የጋሞ፣ የወላይታ፣ ጌዲዮ እና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣ ላይ ከ11-80 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ እና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ እና በትቂት ቦታዎች ላይ ደግሞ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት የሴፕቴምበር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት በተለይም የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የእርጥበት ሁኔታ አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም የነበረው እርጥበት ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች እንዲሁም ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በደቡብ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳር፣ ለመጠጥ ውሃ ሆነ ለጥምር ግብርና ስራ የጎላ ጠቀሜታው ነበረው። በአንፃሩ በተከታታይ እርጥበት እያገኙ ባሉ አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት፣ በአንዳንደ አካባቢዎችም የሰብል በሽታና ተባይ እንዲሁም የአረም መስፋፋት በሰብሎች እድገትና ምርታማንት ላይ መጠነኛ ጉዳት አስከትሏል (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው እና በታቻኛው አባይ፣ በላይኛው ኦሞ ጊቤ፣ አዋሽ እና ባሮ አኮቦ ተፋስሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰትን በመጨመር ወደ ግድቦች የሚገባውን ውሃ መጠን በመጨመር የተሻለ የውሀ ሀብት ከምችት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው ኦጋዴን፣ አፋር ደናከል፣ አይሻ፣ መካከለኛው እና ታቻኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ እና በታቻኛው አዋስሽ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚቀንስ በመሆኑ ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በሂደት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ያገኛሉ። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ ከሁለተኛው ሳምንት ጀምሮ እየተዳከሙ ስለሚመጡ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭትም ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡


Ethiopian Meteorology Institute

## 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እንደሚጨምር ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በአብዛኛዎቹ የበጋ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡ ፡ ካርታ 6 እና 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 21-30, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ

የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ቦረና ምስራቅ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኘዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በሚቀጥሉት የኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በአብዛኛው በደቡብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የጀመረው የክረምት ወቅት ዝናብ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት | • የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በመጠቀም ትርፍ ውሀን ከማሳ ላይ ማሶገድ<br>ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | | ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ |
| የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት<br>• ለቋሚ ተክሎችና እድገት | • የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | • ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ቦረና ምስራቅ ዞኖች የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ እና ባስኬቶ፣ የኤረር፣ ጃረር፣ ነነብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የሴፕቴምብር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጠበቃል። ሆኖም የመስከረም ወር የክረምቱ ወቅት ማብቂያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ወቅት የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት በሚቀንስባቸውና ውሃ አጠር በሆኑ ቦታዎች ላይ የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት ሊኖር የሚችለው መልካም ዕድሎችን በላቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋልም ሆነ ተያያዥ አሉታዊ ተጽኖዎችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በየደረጃው መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| የአባይ፣ የባሮ አኮቦና የኦሞ ጊቤ ተፋሰስ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | •የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር<br>•የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መጨመር<br>•የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል | •የወንዞች መሙላት<br>•በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፊ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• የጎርፍ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• ወራጅ ውኃን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም |
| በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤና አዋሽ ተፋሰስ | ከቀላል እስከ መካከለኛ እርጥበት | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ<br>• በከፍተኛ ሁኔታ የሙሉ ግድቦች ላይ የነበረው ጫና መቀነስ | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ አጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናበ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |
| የዋቤ ሸበሌ ተፋሰስ | ቀላል መጠን | • የጎርፍ ሰጋት አለመኖር | | |